የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፮
አዲስ አበባ ኅዳር ፬ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.56
ADDIS ABABA November 13th, 2018

<u>ማውጫ</u>

ደንብ ቁጥር ፬፻፳፱/፪ሺ፲፩

የሊድ ቀለምን ለመቆጣጠር የወጣ የሚኒስትሮችምክር ቤት ደንብ………………………………………………ገጽ፲ሺ፬፻፴

CONTENT

Regulation No.429/2018

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO CONTROL LEAD IN PAINT……………………page 10430

ደንብ ቁጥር ፬፻፳፱/፪ሺ፲፩

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፱/፪ሺ፲፩

## የሊድ ቀለምን ለመቆጣጠር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፫፻/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፳ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የሊድ ቀለምን መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፱/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪.ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩ በአዋጁ አንቀፅ ፪ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፪/ "ቀለም" ማለት ቫርኒሽን፣ ላኪየርስ፣ ስቴይንስ፣ ኤናሜልስ፣ ግላዝስ፣ፕሪመርስ ወይም ማንኛውም

Regulation No. 429/2018
Council of Ministers Regulation No 429/2018

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO CONTROL LEAD IN PAINT

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 and Article 20 of the Environmental Pollution Control Proclamation No. 300/ 2002.

## SECTION ONE
## GENERAL

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Lead in Paint Control Council of Ministers Regulation No. 429/2018".

**2. Definition**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ Definitions provided for under Article 2 of the proclamation shall be applicable to this Regulation.

2/ "paint" means varnishes, lacquers, stains, enamels, glazes, primers or coatings used for

ለቅብ አገልግሎት የሚውል ሲሆን እና በዋናነት የሬዚንስ፣ ፒግመንት፣ ፊለርስ፣ ሶልቨንትስ እና ሌሎች አድቲቨስ ድብልቅ/ ቅይጥ ነው፤

፫/ "የሊድ ቀለም" ማለት አንድና ከአንድ በላይ የሊድ ውህድ የተጨመረበት ቀለም ሲሆን በሊድ ካርቦኔት፣ ሊድ ክሮሜት፣ ሊድ ክሮሜት ኦክሳይድ፣ ሊድ ክሮሜት ሞሊብዴት ቀይ ሰልፌት፣ ቢጫ ሊድ ሰለፈሮክሮሜት፣ ሊድ ፪ ኤታይልሄክሶኔት፣ ሊድ ሞሊብዴት፣ ሊድ ናፍቴኔት፣ ሊድ ናይትሬት፣ ሊድ ሞኖኦክሳይድ፣ ሊድ ኦክሳይድ፣ ሊድ ኦክታኔት፣ ሊድ ፐርኦክሳይድ፣ ሊድ ሰልፌት እና ትራይ ሊድ ባይካርቦኔት ዳይሀይድሮኦክሳይድ ይጨምራል፤

፬/ "ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች" ማለት የሕፃናት አሻንጉሊቶች፣ የቤት ውስጥና የውጪ የሕፃናት የመጫወቻ ዕቃዎች፣ የሕፃናት መጽሐፍት፣ የስዕል መሣሪያዎች፣ የቤት ቁሳቁሶችና ሌሎች ሊድ ያለው ቀለምን የሚጠቀሙ ምርቶችን ይጨምራል፤

፭/ "የተስማሚነት ምዘና የምስክር ወረቀት" ማለት ሊድ ያለው ቀለም ምርት በዚህ ደንብ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የሊድ መጠን መያዙን በማረጋገጥ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

፮/ "መለያ" ማለት በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተፃፈ፣ የታተመ ወይም በምስል የተቀረፀና በቀለም ቀጥተኛ መያዣና በቀጥተኛ መያዣዎቹ ውጫዊ መያዣ ወይም መጠቅለያ ላይ የተደረገ ወይም ከነዚሁ ጋር የተያያዘ አጠቃላይ የሊድ መጠንን የሚገልፅ መግለጫ ነው፤

፯/ "አጠቃላይ የሊድ መጠን" ማለት የምርቱ ወይም የደረቀው ቀለም አጠቃላይ ሊተን የማይችል ክብደት በመቶኛ መጠን ነው፤

፰/ "አግባብነት ያለው አካል" ማለት በዚህ ደንብ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት በቀለም ውስጥ የሊድ መጠንን ለመቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠው መንግሥታዊ አካል ነው፤

፱/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደየቅደም ተከተላቸው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፩/ በወንድ ጾታ የተገለፀው ድንጋጌ ሴትንም ያካትታል።

any purposes; and is typically a mixture of resins, pigments, fillers, solvents and other additives;

3/ "Lead paint" means paint to which one or more compounds typically added to paint and includes lead carbonate, lead chromate, lead chromate oxide, lead chromate molybdate sulpahte red, lead sulphrochromate yellow, lead 2-ethylhexnoate, lead molybdate, lead naphthenate, lead nitrate, lead monoxide, lead oxide, lead octanoate, lead peroxide, lead sulphate, and tri lead-bicarbonate – dihydroxide;

4/ "Products that use lead in paint as an input" includes children's toys, indoor or outdoor playground equipment, children's books, art materials, home furnishing materials and other products that use lead in paint as an input;

5/ "Certificate of conformity assessment" means a certificate issued to approve a paint product that meets a minimum limit set in this Regulation;

6/ "Label" means a written ,printed or graphic matter on or attached to the immediate container of a paint and the outside container or wrapper of the immediate containers in Amharic or English language about the total lead concentration;

7/ "Total lead concentration" means a weight percentage of the total non-volatile portion of the product or weight of the dried paint film;

8/ "Competent authority" means any governmental body which has mandate to control lead in paint according with this regulation and other laws;

9/ "Ministry and Minister" means the Ministry and Minister of Environment, Forest and Climate Change, respectively;

10/ "person" means any natural person or juridical organ;

11/ "Any expression in the masculine gender includes the feminine.